# ለበርጩማ ኣልቃሹ!

## ከዓሣዬ

ሥልጣን በልመና ፣ ህልሙ ቅዠት ሲሆን
ተሥፋው እንደ ጤዛ ፣ እንዲህ በኖ ሲተን
በግልጽ ወጥቶ ሲታይ ፣ መርዝ ቀላቅሎ ኣጉራሹ
መሆኑ ሲታወቅ ፣ ሣጥናኤል ትንሹ
ታድያማ!
ግዑዙን ይመስል ፣ ሕሊና የለሹ
የታሪክ ኣተላው ፣ ለሆድ ተልክሥካሹ
ለግል ጥቅሙ አድሮ ፣ ትግልን አልፈሥፋሹ
ኧረ ኣሁንሥ ያብቃ ፣ ለበርጩማ ኣልቃሹ ።

እስቲ እንቀራረብ ፣ ለህዝባችን ብለን
ኢትዮጵያዊው ሁሉ !
የበርጩማን አልቃሽ ፣ በሞተበት ቀብረን
ባራቱም ማዕዘናት ቶሎ ተሰባሥበን
እውን ሃይል ያለውን ፣ በቶሎ ኣጠናክረን
ወያኔን በመጣል ፣ ከሥሩ መንግለን
ቁም ነገር እንሥራ ! ኣገር ሣይበተን! ።

ለቁርጥ ቀን ታጋዩ ፣ ያገር ቤቱ ኣንበሣ
እሱ ሕይወቱን ሲሰጥ ፣ እኛ ለኪሥ ሣንሣሣ
ግን ፣
በርጩማን አምላኪ ፣ ያን የትግል ነቀርሣ
ለወያኔ ዕድሜ ቀጣይ ፣ ላገር አምጪ ኣበሣ
ውሾን ውሾ ብለን ፣ ታጥቀን እንነሣ!
በታሪክ ኣሥወቃሽ፣
ለቀጣዩ ትውልድ ፣ እንዳንተው ጠባሣ! ።

በሠላም እየማልን ፣ ሠላምን ሲገድሉ
ኣገር እንደ ዳቦ ፣ ቆራርሰው ሲጥሉ
በዘር በሃይማኖት ፣ ሲገነጣጥሉ
ባላገሩን ሲያደርግ ፣ ባይተዋር ላገሩ
ባዕዱ እያረሰ ፣
መኸሩን ሲጭነው ፣ ከትውልድ ኣገሩ፣
የሴት እህቶቻችን ፣
አንገታቸው ሲቀላ ፣ በየዓረብ አገሩ
እንደ ሸቀጥ ዕቃ ፣
ህጻን ልጆቻችን ፣ ሲሸጥ በዶላሩ
ከእንግዲህ ምን ቀረን?
ለበርጩማ ኣሽርጋጅ ፣ ይብቃን ማላዘኑ ።

በረሃብ እንደ ቅጠል ፣ ሲረግፍ ወገናችን
በባዕድ ከተገረፍን ፣ በገዛ ኣገራችን
ህገ ወጥ ከሆነ ፣ ሰንደቅ ዓላማችን
ለሟች በርጩሜዎች ፣ ነፍሥ ይማሩን ትተን
ፋኖ ኣትነሣም ወይ ፣ ይሁን ጥያቄኣችን?
ኧረ ! ኣሁንሥ በቃን ! ይገባል መልሣችን!
የኣገር ኣድን ኣዋጅ ፣ ክተት ነው ጥሪአችን!
እንደ ኣያት ቅድመ ኣያት ፣ እንደ ኣባቶቻችን! ።

07/11/2010

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.